አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፷፰
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፱ ቀ ፪ሺ፰ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Eighth Year No. 68
Addis Ababa November 9, 2015

ማውጫ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ ደንብ……………………………..…………ገፅ ፩

CONTENTS

**Addis Ababa City Government General Education Quality and Relevance Control Agency Regulation………….............Page 1**

## ደንብ ቁጥር ፷፰/፪ሺ፰
## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የአጠቃላይ ትምህርት ተደራሽነት ጥራት አግባብነት የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የመንግሥትም ሆነ የግል ትምህርት ተቋማትን ብቃት በመገምገም ጥራትን ለመቆጣጠርና ብሎም ወቅቱ በሚጠይቀው መጠን እንዲሻሻል ለማድረግ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

## Regulation No. 68/2015
## A Regulation to Provide for the Establishment and Working Procedures of the Addis Ababa City General Education Quality and Relevance Regulatory Agency

**Whereas,** it is found necessary to establish a system to control accessibility and quality of general education by evaluating competency and quality of governmental as well as private educational institutions and thereby cause improvement compatible to the current situation;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የከተማ አስተዳደሩ የአጠቃላይ ትምህርት አግባብነትና ጥራትን በማስጠበቅ ትምህርት ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊ እና ለፖለቲካዊ ዕድገት እንዲሁም በግሎባላይዜሽን ዘመን ያለውን ውድድር ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወንና ያለባቸውን ሰፊ የጥራት ማስጠበቅ ኃላፊነቶችን ለመወጣት እንዲቻል ከተለመደው አሰራርና አደረጃጀት የተለየና የራሱን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ አወቃቀር በማስፈለጉ፤

በከተማችን የትምህርትን ተሳትፎ ተደራሽ ለማድረግ እና ጥራት የማስጠበቅ ስራው ቀጣይነት ያለው ተግባር በመሆኑና ይህም በከተማ አስተዳደሩ የልማት ዕቅድ ላይ የተመለከተ በመሆኑ፤

በሁሉም የትምህርት ተቋማት የተደራጀ የውስጥ ጥራትና አግባብነት ማረጋገጫ ስርዓት እንዲዘረጋ የማበረታታትና የመደገፍ ተግባር ወቅቱ የሚጠይቀዉና አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአጠቃላይ በከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት የተሰጠውን የትምህርት ጥራትና አግባብነት ማስጠበቅ ሥራ ከግብ ለማድረስ እንዲቻል ኤጀንሲ ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የተማው ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫(፩) (ረ) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**Whereas,** it is found necessary to have a structure different from the usual structure and procedure considering the existing situation to enable education contribute to economic, political and social growth as well as effectively perform the competition in the era of globalization and discharge the responsibilities of extensive quality by maintaining general education relevance and quality;

**Whereas,** it is continuous task to make educational participation accessible and maintain quality and this is stated in the development plan of the City Government;

**Whereas**, it is found necessary and timely to encourage and support towards putting in place organized internal quality and relevance assurance procedure in all the educational institutions;

**Whereas**, it is found necessary to establish an agency to be able to accomplish the task of maintaining educational quality and relevance, which is given special attention, within the City Government;

**Now, therefore,** the City Cabinet has issued this regulation in accordance with Article 23(1) (f) of the Revised Charter Proclamation No. 361/2003, as follows.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፷፰/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "**አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "**አዋጅ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፯ ነው፤

፬. "**ቢሮ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፤

፭. "**ኤጀንሲ**" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ ነው፤

፮. "**የትምህርት ተቋም**" ማለት የግል፣ የሕዝብ፣ የመንግሥት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ የትምህርት ተቋም ሲሆን ከአፀደ ህጻናት፣

## SECTION ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government General Education Quality and Relevance Regulatory Agency Establishment Regulation No. 68/2015".

### 2. Definition

Unless the context otherwise requires, in this Regulation:

1. **"City"** means the City of Addis Ababa;
2. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Proclamation"** means the revised proclamation of Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Reestablished Proclamation No. 35/2014;
4. **"Bureau"** means the Addis Ababa City Government Bureau of Education;
5. **"Agency"** means the Addis Ababa City Government General Educational Quality and Relevancy Regulatory Agency;
6. **"Educational Institution"** means any kindergarten, primary school, secondary school, preparatory and non-formal education of the government, public,

እስከ መሰናዶ እና መደበኛ ያልሆኑትን የሚያጠቃልል የትምህርት መርሃ ግብር እና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ነው፤

private and non-governmental entities established to render educational services;

፯. **"አጠቃላይ ትምህርት"** ማለት የአፀደ ህጻናት የመጀመሪያ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ ትምህርትን ያጠቃልላል፤

7. **"General Education"** includes kindergarten, primary school, secondary school, preparatory and non-formal education;

፰. **"የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ"** ማለት የሥርዓተ ትምህርቱን ዓላማ፣ መርሆዎችን፣ ግቦችንና ፕሮግራሞችን ያካተተ መሪ ሰነድ ነው፤

8. **"Curriculum framework"** means an educational document including objectives, principles, goals, and programs;

፱. **"መርሃ-ትምህርት"** ማለት የትምህርት ዓላማዎችን፣ ይዘቶችን፣ የማስተማር ዘዴዎችን፣ ምዘናና የክፍለ ጊዜ ብዛት ርዝመትን የሚያሳይ ሰነድ ነው፤

9. **"Curriculum"** means a document indicating the objectives, contents, pedagogies, evaluation number and length of period;

፲. **"የትምህርት አግባብነት"** ማለት ከማህበረሰቡ ፍላጎት ጋር በማስተባበር በራሱ የሚተማመን ዜጋ የልማት ኃይል ለመፍጠር የሚያስችል ነው፤

10. **"Educational Relevance"** means an education enables to interlink the community with its demand in a bid to produce self-confident and development force citizen;

፲፩. **"ትምህርት ስታንዳርድ"** ማለት ሁሉንም በአሰራር ስርአትና በተገኘ ዉጤት ላይ ለመለካት የተቀመጠ መስፈርት ነው፤

11. **"Educational Standard"** means criterion stipulated with a view to measure all based on work procedure and the result achieved;

፲፪. **"ውጤት "** ማለት በመማር ማስተማር ሂደት ወይም በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ መስተጋብር የሚመጣ የተማሪዎች የእውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት አዎንታዊ ለውጥ ነው፡፡

12. "**Output"** means acquired knowledge, skill and attitudinal change of students as a result of teaching and learning process or day-to-day activity interaction.

፫. **የፆታ አገላለፅ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለፆች ለሴት ፆታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፬. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሁሉም ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

፭. **መቋቋም እና ተጠሪነት**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ መንግስታዊ መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለትምህርት ቢሮ ይሆናል፡፡

፮. **ዋና መሥሪያ ቤት**

፩. የኤጀንሲ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፤

፪. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተማዉ ክፍሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ይቋቋማል፡፡

3. **Gender Reference**

Unless otherwise expressed in this Regulation, expressions stated in the masculine gender shall apply to the feminine gender.

4. **Scope of Application**

This regulation shall be applicable to all educational institutions within the City Government.

## SECTION TWO

## ESTABLISHMENT, OBJECTIVE, ORGANIZATION, POWER AND FUNCTIONS

5. **Establishment and Accountability**

1. The Addis Ababa City Government General Education Quality and Relevance Regulatory Agency hereinafter referred to as **“Agency”** is hereby established as a government institution having its distinct legal personality;
2. Accountability of the Agency shall be to the Bureau of Education.

6. **Head Office**

1. Head office of the Agency shall be at the city center;
2. Branch offices shall be established in parts of the City, where it is found necessary.

## ፯. ዓላማ

የኤጀንሲው ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ጥራት፣ የትምህርት ተቋማት ስታንዳርድን፣ የትምህርት ተቋማት ድርጅታዊ ብቃት እንዲሁም የሚሠጠው የትምህርት አገልግሎትን ለማህበረሰቡ እና ለሀገሪቱ ተስማሚ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

## ፰. የኤጀንሲው አቋም

ኤጀንሲው፡-

፩.ጠቅላላ ጉባዔ፤

፪.ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እንዲሁም

፫.ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፱. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. በትምህርት ተቋም የሚሠጥ ትምህርት፣ ከሀገሪቱና አስተዳደሩ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ሥርዓተ ትምህርት፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

፪. አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት በህግ የተቀመጠውን የትምህርት ስታንዳርድ፣ የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት ማሟላታቸውን እንዲሁም አግባብነቱና ጥራቱ ደረጃውን ጠብቀው መፈፀማቸውን ይከታተላል፤

## 7. Objective

Objective of the Agency shall be to ensure the quality of education, standard and institutional competence of educational institutions as well as the compatibility of education service rendered to the society and the country.

## 8. Organization of the Agency

The Agency shall have:

1. General Assembly;
2. General Director and Deputy General Directors; and
3. Other necessary staff.

## 9. Power and Functions of the Agency

The Agency shall have the following powers and functions፡

1. Ensure, Supervise and take necessary measures that the education offered by an educational institution is compatible with the curriculum, policy and strategy of the social need and economic demand of the country as well as the City Government;
2. Follow up that generally educational institutions fulfill the educational standards set by law, requirements of education service rendering, as well as the relevancy and quality of education is up to expected level;

፫. አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፬. የአስተዳደሩ የአጠቃላይ የትምህርት ተቋም ጥራትና ብቃት የሚጠናከርበትንና የሚስፋፋበትን ጥናትና ምርምር እንዲሁም የፖሊሲ ሀሳብ ያመነጫል፤

፭. ቁጥጥር የሚደረግባቸውን አጠቃላይ የትምህርት ተቋማትን በሚመለከት የመረጃዎች ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

፮. የአጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ብቃት እና ምዘና መከታተያና መገምገሚያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፯. ፈቃድ ሳያገኙ ወይም የትምህርት አገልግሎቱን ጥራታቸው ከስታንዳርድ በታች በሆኑና በሚሰጡ ተቋማት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

፰. ለትምህርት ተቋማት ዕውቅና ይሰጣል እውቅና አግኝተው የሚሠሩ ትምህርት ቤቶች በሀገር ደረጃም ሆነ በከተማ ደረጃ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

፱. በትምህርት ተቋማት የህብረተሰቡን ተሳትፎ ሊያረጋግጡ የሚችሉ አደረጃጀቶች፣ የወላጅ፣ የተማሪ፣ የመምህራን ፎረም፣ የተማሪ ክበባት ስለመኖራቸው እንዲሁም የትምህርት አገልግሎት ክፍያዎች የወላጆችን የመክፈል አቅም ባገናዘበ መልኩ መከናወኑን ያረጋግጣል፤

3. Issue, renew, suspend and revoke the general competence certificate of educational institutions;

4. Generate policy idea as well as research and study towards strengthening and expansion of quality and competence of general educational institution of the City;

5. Serve as an information center regarding general educational institutions subject to supervision;

6. Establish and implement supervision and evaluation system to follow up competency and assessment of the general educational institutions;

7. Take measures against unlicensed institutions or those which render service below minimum standard of educational service;

8. Give accreditation to educational institutions and ensure that those accredited educational institutions fulfill the educational relevance and quality standards set out under regulations and directives issued both at national and city level;

9. Ensure that educational institutions have organized the necessary structures which ensure participation of the community such as parents, students, teachers' forum and students' clubs and ensure that educational service fee is implemented taking into account paying capacity of parents;

፲. በከተማ አስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች ህግ መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

፲፩. አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በከተማዉ ዉስጥ በማደራጀት አስፈላጊዉን የሰዉ ኃይልና ግብአት በማሟላት ሥራዎችን ይከታተላል፤ ይመራል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

፲፪. በፌደራል መንግሥት፣ በከተማዉ አስተዳደርና በትምህርት ቢሮ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እንዲሁም በሚመለከተዉ አካል የተቀመጡ የትምህርት ስታንዳርዶች አግባብነትና የጥራት ደረጃዎች በትምህርት ተቋማት በተጣሱና ባልተሟሉ ጊዜ አስፈላጊዉን ጊዜያዊና ቋሚ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ በዚህም በተማሪዎች፣ በወላጆችና መንግሥት ላይ ጉዳት ያደረሰ ግለሰብ ወይም ተቋም በወንጀልና በፍትሐብሔር ተጠያቂ እንዲሆን ያደርጋል፤

፲፫.የጠቅላላ ጉባዔ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤

፲፬. ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፤

፲፭. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

፲፮. ሌሎች ከአላማው ጋር የተያያዙ ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፲. <u>የጠቅላላ ጉባኤ አባላት</u>

የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚመክር በከተማዉ ከንቲባ ሰብሳቢነት

10. Employ, administer and fire employees of the Agency according to the civil service law of the City Government;

11. Establish branch offices within the City and follow up and direct the activities upon fulfillment of the necessary human and material resources; details shall be determined by directive;

12. Take the necessary temporary and permanent measure in case where the proclamations, regulations and directives issued by the Federal Government, the City Government or Education Bureau, as the case may be, as well as educational standards, properness and quality levels set by the concerned body are violated or not fulfilled by educational institutions; cause any individual or institution who caused damage to students, parents, and government be criminally or civilly liable;

13. Serve as secretariat of the general assembly;

14. Charge fee for the services it renders;

15. Own property; conclude contract; sue and be sued in its own name;

16. Perform other legal duties related to its objective.

## 10. <u>Members of the General Assembly</u>

The general assembly which deliberates on issues related to general education quality and relevancy, being chaired by Mayor of the City, and composed of representative

የሚመራ የሚከተሉት አባላት የሚኖሩበት ጠቅላላ ጉባዔ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፩. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ፤

፪. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ተወካይ፤

፫. የከንቲባ ጽህፈት ቤት ተወካይ፤

፬. የትምህርት ቢሮ ሃላፊ፤

፭. የንግድ ቢሮ ቢሮ ኃላፊ፤

፮. የኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ፤

፯. የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ፤

፰. የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ፤

፱. የፍትህ ቢሮ ኃላፊ፤

፲. የጤና ቢሮ ኃላፊ፤

፲፩. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ኃላፊ፤

፲፪. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ፤

፲፫. የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ፤

፲፬. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ፤

፲፭. የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነር፤

፲፮. የእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ፤

፲፯. የእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ፤

፲፰. የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት፤

፲፱. የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ፕሬዚዳንት፤

፳. የግል ትምህርት ቤቶች ማህበር ፕሬዚዳንት፤

members from the following institutions is hereby established by this Regulation:

1. Representative of Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education;
2. Representative of Federal Democratic Republic of Ethiopia Trade Competition and Consumer Protection Authority;
3. Representative of Office of the Mayor;
4. Head of Education Bureau;
5. Head of Trade Bureau;
6. Head of Industry Bureau;
7. Head of Culture and Tourism Bureau;
8. Head of Communication Affairs Bureau;
9. Head of Justice Bureau;
10. Head of Health Bureau;
11. Head of Land Development and Management Bureau;
12. Head of Labor and Social Affairs Bureau;
13. Head of Women and Children Affairs Bureau;
14. Head of Youth and Sport Bureau;
15. Commissioner of Addis Ababa City Police commission;
16. Chief Executives of each sub city;
17. Head of each sub city education office;
18. President of Addis Ababa Teachers' Association;
19. President of Addis Ababa Chamber of Commerce;
20. President of private schools' association;

፳፩. የአዲስ አበባ ወጣቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት፤

፳፪. የአዲስ አበባ ሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት፤

፳፫. የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ፎረም ሰብሳቢ፤

፳፬. የኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር፤

፳፭. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወላጅ፣ ተማሪ፣ መምህራን ህብረት ሰብሳቢ፤

፳፮. ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ በከንቲባዉ የሚሰየሙ አባላት፡፡

## ፲፩. <u>የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

ጉባዔው ፡-

፩. ኤጀንሲውን በፖሊሲና ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤

፪. እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፤

፫. የኤጀንሲው ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርትና ሌሎች መረጃዎች ላይ በመመሥረት አስተያየቶችን ያቀርባል፡፡

## ፲፪. <u>የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች</u>

፩. የጠቅላላ ጉባዔው መደበኛ ስብሰባ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሆናል ሆኖም አስቸኳይ ስብሰባ ሲያጋጥም በሰብሳቢው ሊጠራ ይችላል፤

፪. ከጠቅላላ ጉባዔ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

21. President of Addis Ababa Youth Federation;

22. President of Addis Ababa Women Federation;

23. Chairperson of Addis Ababa Residents' Forum;

24. General Director of the Agency;

25. Chairperson of Addis Ababa Parents, Student Teacher Union;

26. Other members to be nominated by the Mayor as may be necessary.

## 11. <u>Power and Function of the General Assembly</u>

The assembly shall:

1. Advise the Agency on policy and strategic issues;

2. Establish technical committees, as may be necessary;

3. Submit opinions on the annual performance report and other information of the Agency.

## 12. <u>Meeting of the General Assembly</u>

1. Regular meeting of the general assembly shall be twice in a year; however, the chairperson may call an extraordinary meeting in case of emergency;

2. There shall be quorum where more than half of the members are present;

፫. የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ያልፋል ሆኖም ድምፅ እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤

፬. ጠቅላላ ጉባዔዉ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ውስጠ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፫. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩. ዋና ዳይሬክተሩ በከንቲባዉ የሚሾምና ተጠሪነቱ ለቢሮዉ ሆኖ ኤጀንሲውን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

፪. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ. በዚህ ደንብ አንቀፅ ፱ የተመለከተውን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤ መፈፀማቸዉንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ. የኤጀንሲውን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ. ኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

መ. እንደአስፈላጊነቱ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ይከታተላል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

3. Decision of the general assembly shall be passed by majority vote; however, in case of a tie, the chair person shall have a casting vote;

4. The General Assembly may issue internal regulation of its meeting procedure.

## 13. The Power and Functions of the General Director

1. The General Director, being appointed by the Mayor and accountable to the Bureau, shall lead and administer the Agency;

2. Notwithstanding the provisions stated under sub article (1) of this Article, the General Director shall:

a. Implement the powers and functions of the Agency stated under Article 9 of this regulation; follow up and control their implementation;

b. Prepare the annual plan and budget of the Agency and submit same to the appropriate organs; implement same up on approval;

c. Withdraw money according to the approved budget and performance plan of the Agency;

d. Follow up, direct, and control the branch offices to be established as may be necessary;

ሠ. ኤጀንሲው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

፫. ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ወይም በሙሉ ለኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## ፲፬. የምክትል ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባራት

፩. ምክትል ዳይሬክተሮች በከንቲባዉ ይሾማሉ፤ ተጠሪነታቸዉም ለዋና ዳይሬክተሩ ይሆናል፤

፪. የኤጀንሲዉን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳሉ፤

፫. በኤጀንሲው መዋቅራዊ አደረጃጀት ጥናት መሰረት ተለይተው የሚሰጣቸውን የስራ ክፍሎች ይመራሉ፤

፬. በስራቸዉ የተመደቡትን የስራ ዘርፎች የአፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅተዉ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባሉ፤

፭. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ወይም መስራት በማይችልበት ጊዜ ተለይቶ የተወከለዉ ይሰራል፤

፮. ከዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

e. Represent the Agency in all relationships it has with third parties;

3. The General Director may delegate his powers and functions to the Deputy General Directors of the Agency to the extent necessary to facilitate its operation.

## 14. Powers and Duties of the Deputy Directors

1. The Deputy Directors shall be appointed by the Mayor and shall be accountable to the Director General;
2. They shall assist the Director General in planning, organizing, directing and coordinating the functions of the Agency;
3. They shall lead departments specifically entrusted to them in accordance with the organizational structure of the Agency;
4. Prepare and submit to the Director General performance report of departments they lead;
5. The Deputy Director specifically delegated shall substitute the Director General in case of absence or incapacity of the latter;
6. Perform such other functions designated by the Director General.

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፭. የበጀት ምንጭ

የኤጀንሲው በጀት በአስተዳደሩ ይመደባል፡፡

### ፲፮. ስለሂሳብ መዛግብት

፩. ኤጀንሲው በከተማዉ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት መሠረት የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

### ፲፯. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ መከበር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፲፰. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ይህንን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ቢሮዉ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፲፱. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ፣ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## SECTION THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 15. Budget Source

Budget of the Agency shall be allocated by the Government.

### 16. Books of Account

1. The Agency shall keep complete and accurate books of account in accordance with the financial administration system of the City Government;
2. The books of accounts and financial documents of the Agency shall be audited annually by the City General Auditor.

### 17. Duty to Cooperate

Any person shall be duty bound to cooperate for the implementation of this Regulation.

### 18. Powers to Issue Directive

The Bureau may issue directives for the implementation of this Regulation.

### 19. Inapplicable laws

Any Regulation, directive or customary practice which is inconsistent with matters covered by this Regulation shall have no effect.

**፳. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጥቅምት ፳፱ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**20. Effective Date**

This Regulation shall enter in to force as of 10th of November 2015.

**Done at Addis Ababa**

**On this 9th Day of November, 2015**

**Diriba Kuma**

**Mayor of Addis Ababa City**